የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር፣ገበሬ፣ነጋዴ፣ወታደር፣ምሁር— መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የመላ ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ /መ.ኢ.ሶ.ን./ ልሣን

ቁጥር 43
ሐምሌ 1፣1968

ከሃዲ ምሁራንና ፀረ አብዮት ተገላቸው

“ማንኛውም አብዮት፣በርግጥ አብዮት ከሆነ፣የመደቦችን መሸጋሸግ ያስከትላል። በእውነትም ሰፊውን ሕዝብ ለማንቃትና በአብዮት እያሸፈ ሕዝቡን የሚደልሉትን ኃይሎች ለመታገል ከተፈለገ በአብዮት ሂደት በታቸውን የለወጡትን መደቦች መርምሮ መጠቆም ያስፈልጋል።”
/ሌኒን፣'ል ከሳስ ሸፍት'፣ሙሉ ሥራዎች ቅጽ 25፣ገጽ 130/

የየካቲት አብዮታዊ እንቅስቃሴ ያስከተለው እንደዚህ ዓይነቱ የመደቦች መሸጋሸግ ዛሬ እየሰከነ የሚሄድበት ወቅት ነው። በዚህም የተነሳ የአብዮቱ ወዳጆችና ጠላት በግልፅ እየተለዩ፣ በአገራችን የተፋጠጡት ሁለት የጠላት ሰፈሮች ለወሳኙ ፍልሚያ ኃይሎቻቸውን በመሰብሰብ ላይ ናቸው።

እውነተኛ ሕዝባዊ አብዮት ረዥምና መራራ ነው። በዚህም ረዥም አብዮታዊ ጉዞ መንገዱን አብሮ የጀመረ ሁሉ አብሮ አይዘልቅም። ገና ከመንደርደሪያው፣ወይም ከመሃል...ባቡሩ በየቦታው እየተንጠባጠቡ የሚቀሩ ብዙ ናቸው። ከነዚህ መንገድ ቀሪዎችም መሃል የተወሰኑት ከፍል እኩን አጥፍ ለመቆየት ቢችሉም አብዛኞቹ አብዮትን በመክዳት ብቻ አይወሰኑም። ቀድሞ ተንከባ መንገዱ አብረዋቸው በነበሩት ላይ፣በመቀጠለው በአብዮቱ የወደፊት ጉስጋሴ ላይ አደጋ ለመጣል ያሴራሉ፣ ይፍጨረጨራሉ። ነገር ግን የታሪክ ጉማ ቻንም ቢሆን ወደፊት ተጓዥ ነውና እነዚህ ከሃዲዎች በሚጥሉበት አደጋ አይገታም። እንዲያውም መንገድ ቀሪዎቹ በታሪክ ጉዞ ተወፍልቀው ትቢያ ሆነው ይታለፋሉ።

በአብዮታዊ እንቅስቃሴ ወቅት ሃቀኛ አብዮታውያን በየጊዜውና በየትግሉ ደረጃ ከአብዮቱ የሚከናበቱትን ከፍል ሳይገነዘቡ በሆነ መንገድ ተንትነው በጥንቃቄ መርምረው ከደረሱበት ወዳጅና ጠላትን በግልፅ ለይተው ትግሉን ወደፊት ማራመድ ይችላሉ። በቅድሙ አብዮት ያደረጉትን፣ የአብዮቱ ማዕበል በታትና ከታሪክ በተወዘከር ሲወረውሩ ልብ ይሉትን ያረጀ ያፈጀ የመደብ ትንተና ቸውን የሙጥኝ ይዘው አንገኝ ካሉ ግን፣ የትላንት የትግል ጓድ ዛሬ ከጠላት ሰፈር ተደባልቆ እነሱኑ ሊያጠፋ የሚያደርገውን ትግል ሊረዱ አይችሉም። ሕያው የሆነና የአብዮትን የእድገት ደረጃ የተከተለ ትንተና ማድረግ ተስኗቸው ወዳጅ ከጠላት በተደበላለቀበት ትርምስ የተዘረከረከ ትግላቸው ረቂቅ ባይ ሄድ ወድቆ ይከሰከሳል።

በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያችን የኃይለ ሥላሴን አገዛዝ የሚቃወሙ መዓት ኃይሎች ነበሩ። እስከተወሰነ ደረጃም ድረስ ቢሆን የነቁ መሳፍንት/ኢንላይትንድ አሪስቶክራትስ/ አቅባይ ከበርቴ ያቸና ትናንሽ ባላባቶች፣ከዚያም ብሄራዊ ከበርቴው፣መቀሳሰው ንዑስ ከበርቴ፣ወዛደሩና ገበሬው ተመያለው የኃይለ ሥላሴን አገዛዝ በተለያየ ደረጃ ይቃወሙ ነበር። የየካቲት ከፈነዳ ጊዜም በተገኙት የሕዝብ ድሎች፣የገጠር መሬት የሕዝብ መሆን፣የአንዳንድ የማፍሪያና የማከፋፈያ ድርጅቶች መወረስ፣የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች የመንግስት መሆን፣የብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም መታወጅ...ከላይ ከተጠቀሱት መደቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች አንዳንዶቹን ወቅሰለው ወደ ፀረ አብዮት ሰፈር እንዲነጉዱ አድርጓቸዋል።

“ለውጡን እኮ የተቃወመ የለም፣እነሱ ግን አበዙት” የሚለው አነጋገር መደቦች ትግሉ ከአንድ ደረጃ ሲደርስ ከአብዮቱ ሲለዩበት አምባገር የሚደጋገሙበት አነጋገር ነው። በዚህ መልክ ከትላንት የኃይለ ሥላሴ ተቃዋሚዎች ውስጥ አንዳንዱ ከፀረ አብዮት ሰፈር ተደባልቆ በሕዝብ ተነቅቶበትና ተተፍቶ ከታሪክ ትቢያ መጣያ ተጥሏል። አንዳንዱ ገና አልተነቃበትም። በተለይ አብዮትን የከዳው የንዑስ ከበርቴ ክንፍ ካለፈቸው የተራማጅነት ዘመኑ ባሰየራት ጥሪቱ ተሸፍኖ እስከቅርቡ ጊዜ ድረስ ማወናበድ ችሎ ነበር። ይህም ክንፍ ቢሆን፣ሰፊው ሕዝብ ከነቃ ይነቃል የሚል መደባዊ ስጋት ይዞት የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ጉያ ሕሊናቸው እንዳይቆጠር ብዙ ዓይነት ማወናበድ ቢሞክርም ሳይሳካለት በሴራ ከጥቂት ወራት ወዲህ እየተጋለጠ ነው። ወርቦ ወደ ተፋትና ከታሪክ ትቢያ መጣያ ውስጥ ወደመጣሉ እየተቃረበ ነው።

ይህ ከሃዲ የንዑስ ከበርቴ ክንፍ በኃይለ ሥላሴ ዘመን የአብዮቱ ወገን ብቻ አልነበረም። በተረጋገጠው አለሁ አለሁ፣አትርሱኝ ማለት በለሚያጠቃቅመ ከምርት መሳሪያዎች ጋር ያለው ግንኙነት የላላ በመሆኑ ከሁሉ 'ተወርዋሪ' ይመስል ነበር። ከወዛደር ጓዶችን ይልቅ ውክታና ድንፋታ ይወዳል። ከየካቲት በፊትም ሆነ ከየካቲት በኋላ ለተወሰነ ጊዜ በታላቅ ድንፋታ የትግሉን ራዕታውራሪነት ይዞ ጥቂት የተንገራደደ መደብ ነው። የአብዮቱ ጅራፍ ጩኸት እስከሚደነግጠው ድረስ በአብዮቱ ሰፈር ከሁሉ ጽኑ ታጋይ ባይሆንም ከሁሉ ጯሂ ክፍል ነበር።

ዛሬ፣ከየካቲት ወዲህ የተወሰዱት አብዮታዊ እርምጃዎች ይህን ክፍል አንዳንዴም ተመና ውተውታል። አንዳንዴም ለጥቂት በተውታል። በእውነትም አብዮቱ ከገፋ 'ነገ በኔ' እያለ በቁሙ የሚያንገበግበት ደረጃ አድርሰውታል። ተደራጅቶ ጥቅሙን ለመጠበቅ ባለመቻሉ የወደፊት እድሉ ከጥልቢ ያከመ መቆር በለታየው በትግሉ ውስጥ መላ ቅጡ ጠፍቶታል። ራሱ ተሸብሮ ሌላውን ከማሸበር

በስተቀር ምንም አይታየውም::ዛሬ የኢትዮጵያ ንዑስ ከበርቴ ቀኝ ክንፍ እንቢን የሕዝብ ዱል
ነጋሪት ሲጎሰምበት ይቀርና የገዢ ጥሳው የሚያስደነግጠው የተሳቀቀ ክፍል ሆኗል::የትላንትናው
'ደብዱ'ሁሉ እንዳልነበረ ተረስቶ''ኃይለ ሥላሴ ማረኝ የደርጉስ ነገር ምንም አላማረኝ''
እያለ ቅድመ አብዮት ኢትዮጵያን መስቦ መናፈቅ ጀምሯል::መደቡ ድሮም ቢሆን ታታሪነት፣ቆራጥነ
ትና ትዕግስት የማይወድለት መደብ በመሆኑ'ከማያውቀት መለአክ የሚያውቀት ሰይጣን ይሻላል'በ
ሚል ፈሊጥ ከኢምፔሪያሊዝም፣ከፊውዳሊዝምና ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር እየተመሳጠረ ይህን አጠራ
ጣሪ የሆነበትን የአብዮት ጉዞ ለማደናቀፍ ይፈለጋል::በዚህም ታክቲክ ይቀርጥና የአርቀ እቅን
ወደትላንት ደመኞቹ ይዘረጋላቸዋል::

ይህ ክሃዲ ክንፍ በዚህ መልክ ሰፈር ሲቀይር፣ያንኑ አለሁ አለሁ አትርሱኝ የሚለውን
ድንፋታውን ይዞ ቢሆንም በአብዮቱ ሰፈር ሆኖ ያያትን አይቷልና ዛሬ የፀረ አብዮት ኃይሎችን
ፊታውራሪነት ሲይዝም ጩኸቱና ውካታው ቢጨምር እንጂ ከድሮው አይቀንስም::በወዛደሩ ጉን ተሰል
ፍ ድር ሲታገል ዲሲፕሊን ያልተማረ፣መሙህ ሲያሰኘው ዛሬ ከጉኑ ቆመው የሚያራግቡለት መሳፍንት
ና እነ ሲአይኤ የመገፈስ አርጋታ ይሰጡታል ብሎ መገመት አስቸጋሪ ነው::ስለዚህም ትላንት የ
ተራማጆች ወገን ደገፊ ፊታውራሪ የነበረ ንዑስ ከበርቴ ዛሬ የአድሃሪው ወገን ደገፊ ፊታውራሪ
ቢሆን እዳገም አያስገርምም::ይህ የወላዋይ ንዑስ ከበርቴ የማይለየው ምልክቱ ነውና::ሌኒን
እንዳለውም እንዲህ ዓይነቱ ንዑስ ከበርቴ''ታታሪነት፣ድርጅት፣ዲሲፕሊንና ጽናት የለውም እን
ጂ በቀላሉ ከአንዱ ጫፍ ወደሌላው ጫፍ የሚወረወር መደብ ነው::''

ዛሬ በሃገራችን የዚህ ክሃዲ ንዑስ ከበርቴ ክንፍ ፊታውራሪነት የተያዘው'ኢህአፓ'
በተባለው ፀረ ወዛደር ድርጅትና ዲሞክራሲያ በተባለው ጋዜጣው ነው::ይህ ቡድን፣በዛሬው የኢት
ዮጵያ ሁኔታ፣ከደርጉ በስተቀኝ የተሰለፉትን ንዑስ ከበርቴዎችና ሌሎች አድሃሪ ኃይሎች የሚወክ
ል የነሱም ሙሉ ድጋፍ ያለው ቡድን ነው::የዛሬ ኪሳራውን አያርገውና ይህ ቡድን እንዳሁኑ ሳ
ይጋለጥ ብዙ ሃቀኛ ተራማጆችንም አወናብዶ ነበር::የኢትዮጵያን አብዮት በሚመለከቱ ዋና ዋና
ጥያቄዎች ላይ በሙሉ የወሰዳቸው አቋሞች የመሳፍንቱና የነሲአይኤ ቢሆኑም፣እነዚህን አቋሞችን
በግራ መሳይ የነገር አጣጣሉ፣በድንፋታውና በጩኸቱ ሸፍኖ ብዙ ወጣቶችን አወናብዶ ነበር::ነገ
ር ግን የዲሞክራሲያ ቡድን የመደብ መሰረት የተወናበዱ ወጣቶች ብቻ አልነበሩም::ከየኪቲቱ ወ
ዲህ አብዮቱን ከቤተሰባቸውና ከአካባቢያቸው ጋር አብረው የከዱ አድሃሪ ወጣቶች በሙሉ፣ከደርግ
በስተቀኝ ያሉ አድሃሪ ኃይሎች በሙሉ ይህ ቡድን ደርጉን ከነሱ አኩልና ሙሉ በሙሉ ስለሚቃወም
ላቸው በስተጀርባው ተሰልፈው ይገኛሉ::

/በነገራችን ላይ ይህ ቡድን እየተጋለጠ ሲሄድ ከፍተኛ ኪሳራ ውስጥ ይወድቃል::ደር
ጉ አብዮቱን የሚጠቅሙ እርምጃዎች መውሰዱን እየገፋበት ከሄደ፣ዲሞክራሲያ የያዘውን 'የሙሉ ተ
ቃውሞ'አቋም ይዞ መቀየት ዉርስ መጋለጥ ይሆንበታል::ተቃውሞ ለቀንስ ካለ ደግሞ አድሃሪ ወጣ
ቶችና ወቅላላው ከደርጉ በስተቀኝ የሚገኙ የአድሃሪዎች ጥርቃም ሌላ የነቃ አድሃሪ፣ሌላ''ኩ
ከብ''ይፈለጋል::'ቀይ ባንዲራ'የተባለችው በድን ለዚህ የአድሃሪዎች ''ተራማጅ ኩከብነት''
ራሷን በማዘጋጀት ላይ ነች::የዲሞክራሲያ ቡድን ግን የሚቀረው ምርጫ ወይ ያለውን አቋም ይዞ
ዉርስ መጋለጥ፣ወይ አቋሙን ቀይሮ የአድሃሪዎች ድጋፍ ማጣት ነው::በዚህ ቡድን ውስጥ ተወናብ
ደው የተሰለፈ ሃቀኛ ተራማጆች ግልጽ የሆነ ምርጫቸውን በማሳየት ላይ ናቸው::/

ለማንኛውም፣ምንም እንኳ በመደብ ጥቅም ላይ ሃፍረት የሚሉ ነገር ባይኖርም፣የኢትዮጵ
ያ ንዑስ ከበርቴ ቀኝ ክንፍ በዛሬው ፀረ አብዮት አቋሙ አፍሮበታል::ስለሆነም፣ይህ ክሃዲ ክ
ንፍ ከላይ እንዳልነው ምንም በማያጠራጥር ሁኔታ በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ከመሳፍንቱና ከነሲአ
ይኤ ጋር በአንድነት ቢሰለፍም አቋሙን ተራማጅ ኩል እየቀባ ለማቅረብ ይሞክራል::

በኢትዮጵያ ሶሺያሊዝም ታወጀ ሲባል እነ አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ''ኢትዮጵያውያን
በቀድሞ ጊዜ ይታወቁላቸው የነበሩት ነፃነቶች ጥራት በሌለው የኢትዮጵያ ሕብረተሰባዊነት በሚል
ተደመሰሱ'' ብለው መግለጫ አወጡ::የኢህአፓ የውጭ ተጠሪ ሆኖ የሚሰራው 'ዓለም ዐቀፍ የኢት
ዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን'የተባለው የአድሃሪ ወጣቶች ድርጅት''የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁና ጠላት
የኢትዮጵያ ሕብረሰባዊነት ነው''ብሎ አወጀ::እነዲሞክራሲያም ''በኢትዮጵያ ፋሺዝም ነገሠ''
ብለው የበኩላቸውን አስተጋቡ::እነአስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነቅቶ፣
ተደራጅቶና ታጥቆ ሳይደቁሰን እንቅደመው በማለት ''ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግስት እንምረጥ''ይላ
ሉ::የክሃዲዎቹ ቡድን ይህን የቀልባሾች ጥያቄ እንደማይሆን አድርጉ በነሌኒን ስም ሊያቀርብላ
ቸው ተፍ ተፍ ይላል::እነ አስፋ ወሰን ተራማጅ ተማሪዎች ከገበሬው ተዋሃዱበን ብለው ዘመቻው
ን ይቃወማሉ::እነዲሞክራሲያ አሁንም በነሌኒን ስም እየማሉ ''ዘመቻውን መበተን፣መምሪያውን
መዝጋት'' ያስፈልጋል እያሉ በግልጽ በጋዜጣቸው ይጽፋሉ::በገቢርም ዘመቻውን ለመበተን ሞከረ
ው በንቃ ዘማቾች ከፍተኛ ትግል መክሸፋቸው ይታወሳል::እነአስፋ ወሰን የመሬቱን አዋጅ ይቃወ
ማሉ::በውጭ አገር የኢህአፓ ተጠሪ ነኝ የሚለው ፌዴሬሽን አሁንም የነሌኒንን ስም እየጠቃቀሰ
ይህንን አዋጅ የሚቃወመው 'አድሃሪ ስለሆነ፣አድቬንቸሪስት ስለሆነ፣እንዲያውም/ቀደም ብሎ እን
ደጠቀሰው/የኢትዮጵያ ጭሰኛ መሬት ካገኘ ፋሺስት ይሆናል''በሚል ሰበብ እንደሆነ በየጊዜው የ
ሚያወጣቸው መግለጫዎች ያስረዳሉ::

ኢህአፓና መሳፍንቱ አቋማቸው በመሳሰል 'የአጋጣሚ ነገር ነው'እንዳይባል፣በዚሁ ፌዴ
ሬሽን በተባለው ''አገናኝ ድርጅት'አማካኝነት የመሳፍንቱ 'የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሕብረት'
እንደ አፍሪክ አዚ ዓይነቶቹ የሲአይኤ ጋዜጦች፣በገቢር በመተባበር ላይ ናቸው::ኢህአፓ ይህን
ን ፌዴሬሽን የተባለ የነአስፋ ወሰን ግለገል ድርጅትና የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ከሃዲ
ክንፍ 'አብዮታዊ ንቅናቄ'እያለ ያወድሰዋል::ይከራከርለታል::

ታዲያ ይህ ሁሉ ሆኖ የነዲሞክራሲያ ቡድን የዛሬን አያርገውና ለብዙ ጊዜ ''ተራማጅ''
ተብሎ የሚጠረጠርበት ጊዜ ነበር::ለዚህ መቸስ ይህን ቡድን የረዳቸው በአንድ በኩል ይህ ቡድን
የሚወክለው የንዑስ ከበርቴ ክንፍ በአብዮቱ ታልፍና ተተፍቶ ከመሄዱ በፊት የነበረቸው የተራማ

ጅነት ቅርስ ነቸ::በሌላ በኩል ደግሞ ይህ ክንፍ አደባባይ ይዞ በሚወጣው አቋሙ ሁነ አበላ ቶን አንኳ አየሸሸገ በሚያደርጋቸው አጠራጣሪ ግንኙነቶችና ትብብሮች ከአድሃሪያኖች ጋር የተሰላ ፈ ቢሆንም፤ይህንን ሁሉ ለተወሰነ ጊዜ በድንፋታ ለመሸፈን መቻሉ ነው::በተጨማሪም፤ይህ ቡድን በደርግ ተራማጅ እርምጃዎች ላይ ያለውን ተቃውሞ በደርግ አድሃሪ እርምጃዎች እያሳበበ በመቀረ ብ ያካሄደው ቅስቀሳ፤ደርግ በሕዝቡ ትግል ውስጥ ስለያዘው ቦታ ገራ በተጋባው ክፍል ውስጥ ''የደራ ገበያ''ማግኘቱ ነበር::በደርግ ጥያቄ ጥራት እየተገኘ ሲሄድም፤ደርግ ራሱም ከአድሃ ሪ እርምጃዎቹ ቀነሰ፤ከተራማጅ እርምጃዎቹ ጨመር እያደረገ ሲሄድ፤ይህም ''የደራ ገበያ''መቀ ዝቀዙ አልቀረም::

የዲሞክራሲያ ቡድን ይህን ከህደት ሸፍኖ አድሃሪ አቋሞቹንም ሆነ ተጠሪዎቹ በውጭ አ ገር ከነአስፋወሰን ድርጅት ጋር የሚያደርጉትን ትብብር የሚያስደግፈት ''በኢትዮጵያ ውስጥ ያንሰራራው ፋሺስታዊ ሥርዐት ነው''በሚለው ቲዎሪ ላይ ነው::በእርግጥም ይህ ቲዎሪ ለክ ከሀ ነ፤ከሃዲው ቡድን እንደሚለውም፤እነስታሊን ፋሺስቶን ሂትለር ለመቋቋም ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝ ም ጋር ሳይቀር የህብረት ግንባር ፈጥረዋል::እነሆ ቺሚን የጃፓንን ፋሺዝም ለመቋቋም ከቺያ ትናም ወሰፍንትና ከፈረንሳይ ቀኝ ገዥዎች ጋር የሕብረት ግንባር ፈጥረዋል::ስለዚህ የዚህ ከ ሃዲ ቡድን 'ቲዎሪ'የሚያመራውም ዛሬ ''የደርግን ፋሺዝም''ለመዋጋት ከኢትዮጵያ መሳፍንትና ከነሲአይኤ ጋር በህብረት መታገል ይቻላል፤ያስፈልጋልም ለማለት ነው::በርግጥም ይህ አደገኛ 'ቲዎሪ'በነማርክስና በነሌኒን ስም የኢትዮጵያን ተራማጆች በመሳፍንትና በኢምፔሪያሊስቶች ጉን ለማሰለፍ ከሃዲ ምሁራን የጠነሰሱት ሴራ ነው::

የከሃዲ ምሁራኖቹ ቡድን ጠቀላላ ታክቲኩን የቀየሰው በዚህ ''ደርግ ፋሺስት ነው'' በሚል ተለካሽ ቲዎሪ ላይ ቢሆንም እስከዛሬ ድረስ ይህንን ቲዎሪውን ሳይንሳዊ በሆነ ትንተና ማስረዳት አልቻለም::አንድ ጊዜ፤በአንድ ጽሁፉ ላይ፤''የደርግን ፋሺስታዊ ስርዓት''ለማጋለጥ ሞክር 'ፋሺዝም ጥንትም ያው አሁንም ያው ትግልም እንዲሁ'በሚል ርእስ አቅርቦ፡ እንደነበር ይታወሳል::በዚያ አስቂኝ ቀጥር ላይ ''የደርግን ፋሺስትነት''ለማስረዳት ሞክሮ እንዳልተሳካ ለት እንኳን እኛና የከሃዲ ምሁራኖቹ ቡድን እራሱ ተገንዝቦት ነበር::ስለሆነም ''የደርግን ፋሺስትነት''ለማስረዳት'ወደፊት በሰፊው እንመለስበታለን' ብሎ ቃል ቢገባም''ጥናው''ጽሁፉ ሲጠበቅ መንፈቅ ሊሆነን ነው::በዚሁ አንፃር በዚሁ ተለካሽ ቲዎሪ ላይ የተመረኮዘው የከሃዲ ምሁራንና የመሳፍንቱ ትብብር ሥር እየሰደደ ስለሆነው ''ለመቀያ ያህል''በሰጡን ጽሁፋቸው ላይ ተመርኩዘን እኛን ከመሳፍንቱ ጉን የሚያሰልፈን ቲዎሪ ገና እንዳላቀረቡልን እናስረዳለን::

በዚህ ቀጥራቸው ላይ ገና ሲጀምሩ እንዲህ ይላሉ፦

''ስለጊዜያዊ ወታደራዊ መንግስት በተለይም በስልጣን መሰላል የመጨረሻው ርካብ ላይ ስለ ተቀመጡት 'ምርጥ' መኮንኖች በምናወራበት ጊዜ 'ፋሺስታዊነት' የሚለውን ቃል አዘውትረ ን እንጠቀማለን::ይህንን ቃል የምንጠቀመው ጭካኔንና አብሪትን በሚያመለክተው ጠባብ ትርጉም ብቻ አይደለም::ውስጣዊና ይዘታዊ ፅንሰ ሃሳቦችንም አብረን በማገናዘብ ነው:: ከነዚህ ይዘቶች ለዓይነት ጥቂቶችን እንጠቅሳለን::

ከዚህ ጥቅስ መጠርጠር እንደሚቻለው፤''ጭካኔና አብሪት''የፋሺዝምን ላይ ላዩን የሚ ታይ መልክ ሲጠቁም፤''ውስጣዊ ይዘታዊ''የሚለው አነጋገር ደግሞ የፋሺዝምን የኤኮኖሚ መሰረት ለመጠቆም የቀረበ አነጋገር ይመስለናል::ይህንን የምንለው መቸስ ''ማርክሲስት'' ነን ብለው ሲጎረር ስትራክቸሩ/ይሄዳሉ ከሚል ተስፋ ተነስተን ነው:: ወደልባሱ/ወይም ወደ ናልና የፋሺዝምን ስርዐት ኤኮኖሚያዊ መሰረት በሚገባ አሳይተውን ከዚያ

በመሰረቱ 'ትንተናው'መጀመር ያለበት''የኢትዮጵያ ፋሺስት ስርዐት''የቆመበትን የኤኮ ኖሚ መሠረት በሚገባ በማብራራት ነበር::ከሃዲዎቹ ምሁራን ትንተናቸውን 'በአብሪትና በጭካኔ' ሲጀምሩ አንባቢ ትንሽ መጠርጠር ይጀምራል::ካሁን ካሁን ደረሰኩበት እያለ የሚያስበው''የኢ ትዮጵያ ፋሺዝም የኤኮኖሚ መሰረት'' ትንተና እያደር የውሃ ሽታ እየሆነበት ሲሄድ የከሃዲዎቹም ዓላማ የዚያኑ ያህል ግልጽ እየሆነለት ይሄዳል::ቀስ ብሎም ይቀርጥለታል::ይህ ጽሁፍ ከያዘው 8 ገጽ ውስጥ ውስጥ አንባቢው እስከ ገጽ 5 ድረስ ስለፋሺዝም 'ጭካኔና አብሪት'ከተንበለበለ ለት በኋላ፤በድንፋታ ብርታት ያደናገሩት የመሰላቸውን አንባቢ በተለካሻ ሰበቦች ተሰናብተውት፤ ወደሌላ 'ጉዳይ' ያልፋሉ::ስለሆነም የዲሞክራሲያ ቡድን 'ፋሺዝም ሳይንሳዊ ትንተና ሸሸተው በኢትዮጵያ'የሚለይበት ቀንጣት ነገር የለውም::ሁለቱም ፋ በኢትዮጵያ'ከነአስፋወሰን 'ፋሺዝም በኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች ላይ የወረደውን 'ጭካኔና አብሪት'ለማ ሺዝም በኢትዮጵያ ሲሉ ያው በኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች ላይ የወረደውን 'ጭካኔና አብሪትን'በደፈናው መለከት ነው::ችግሩ ታዲያ ''የታሪክ አዋላጅ አመጽ ነው''ብሎ 'ጭካኔና አብሪትን'በደፈናው ሳይሆን 'የየትኛው መደብ ጭካኔና አብሪት በየትኛው መደብ ላይ 'ብሎ ሳይጠይቅ አንድ ከመደብ አንፃር የሚመለከት ተራማጅ የአንድን ሥርዐት መልክ አይወስንም::ይቺን ይቺን ለፋሺስቶቹ የአ ስፋወሰን ክሊክ ይተዋል::

ማንኛውም እንቅስቃሴ መሰረታዊ የሆኑ የኤኮኖሚ ይዘቶች አሉት::ይሸ መቸስ የማርክ ሲዝም ሀሁ ነው::የፋሺዝም ስርዓትም የተወሰኑ የኤኮኖሚ መሰረቶች አሉት::ዛሬ በኢትዮጵያ የ ሚካሄደውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሕያው የሚያደርጉት የኤኮኖሚ መሰረቶችና የፋሺዝም የኤኮኖሚ መሰረቶች አንድ ናቸው ወይ? የዲሞክራሲያ ቡድን እንደሚወተውተን ለነገሩ ያህል ከመሳፍንትና ከ ኢምፔሪያሊስቶች ጋር ተሰልፈን ደርግን ለመዋጋት ብንፈልግ እንኳ ይህንን መሰረታዊ አንድነት ሊነግሩን ቢችል ነበር::

ግን ይህን ሊያደርጉ አይችሉም::ፋሺዝም በመጀመሪያ እንሰራርቶ የታየባቸው አገሮች ጀርመን፤ጣሊያን፤ጃፓን...የዚህ ስርዓት መሰረት ሞኖፖል ደረጃ የደረሰ ካፒታሊዝም ሲሆን፤ደጋፊ ኃይሎቹ ታላላቅ ባለኢንዱስትሪዎች፤ባለባንኮች፤ነጋዴዎችና የመሳሰሉት ናቸው::እንዲህ ዓይነት ስርዓት እንዲመሰረት የካፒታሊስት ስርዓት ከፍተኛ የኤኮኖሚ ክራይስስ ውስጥ ወድቀ ኃይለኛ የ

ወዘደር አንቀስቃሴ ወጥር ይዘት በዚህ የወዘደር ገፅታ የተደናገጠው ታላላቅ ከበርቴ ኑሮው አያሽቀለቀለ በመውረድ ላይ ሆኖ የተበባጠ የንዑስ ከበርቴ ድጋፍ ያስፈልጋል::

እርግጥ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሶስተኛ ዓለም አገሮች በኢምፔሪያሊዝም፣በፊውዳሊስቶችና በቢሮ ከበርቴዎች ትብብር የሚቋቋሙ፣በፋሺስታዊ አመጽ የሚገዙ መንግስታት በአንዳንድ ሕዝቦች ላይ ተጭነዋል::ለነዚህ ምሳሌ ቺሊን፣ኢራንን፣ብራዚልን፣ኢንዶኔዥያን...መጥቀስ ይቻላል::እነዚህ አገዛዞች የተወለዱበትን አካባቢ ብንመለከት አቀባባይ ከበርቴዎች፣ቢሮክራት ካፒታሊስቶች፣ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም ጋር በመመሳጠርና ከሌሎች አድሃሪ ኃይሎች ጋር በመተባበር በነዚህ አገሮች ይካሄዱ የነበረትን ተራማጅ እንቅስቃሴዎች <u>በመቀልበስ</u> በጭቁን ሕዝቦች ትከሻ ላይ የተጫኑ ናቸው::

የነዚህ ፋሺስታዊ አገዛዞች ኢኮኖሚያዊ መለኮች መሬትን ላራሹ ማድረግ ሳይሆን፣እንዲያውም የቀደሟቸውን ተራማጅ የመሬት ስሪቶች በመቀልበስ አርሶአደሩን እየነቀሉ መድረሻ ማሳጣት፣የኢምፔሪያሊስቶችን በሃገሪቱ ኢኮኖሚ ፈላጭ ቆራጭነት ማጠንከር፣የተወረሱ ፋብሪካዎችን ለቀድሞ ከበርቴዎች መልሶ ማስረከብ ወዘተ. የመሳሰሉ ናቸው::

የዛሬው የኢትዮጵያ አብዮት ኢኮኖሚያዊ ይዘት ግን ከነዚህ ፈጽሞ የተለየ ነው::የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በአዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ጉዳና ላይ የሚደናቀፍ ድሎችን ተጎናጽፎ ለነሱ ዋስትና ለመስጠትና ሌሎች ድሎችን ለማግኘት በትግል እፍላ ላይ ነው::የእንቅስቃሴው ይዘት መሬትን ላራሹ ያደረገውን አዋጅና ሌሎች ተራማጅ እርምጃዎችን ዋስትና ባለው ሁኔታ ከሥራ ላይ ለማዋል ነው::

የዲሞክራሲያ ቡድን መሪዎች 'የፋሺዝም ስርዓት በኢትዮጵያ ነግሷል' ሲሉ፣ይህ ዛሬ የተያዘው እንቅስቃሴ በኢኮኖሚ መሰረቱ በምን ፈሊጥ ከፋሺዝም ጋር እንደሚገናኝ ገለጽ አድርገው ማሳየት ነበረባቸው::ግን ይህን ማድረግ አይችሉምና ደፍረው አልገፉበትም::አለገፉበትም እንጂ ሰው ለማወናበድ ግን መሬት ላራሹ የሚባለው ፋሺዝምን ያመጣል ለማለት ቃጥቷቸው ነበር:: በዚህ በኩል ግን ነገሩን ገልጥልጥ አድርጉ የተጋለጠው የኢህአፓ የውጭ ተጠሪ የሆነው የፌዴሬሽን ቡድን ሲሆን ይህ ድርጅት በቀጥታ የየካቲት 25/67 አዋጅ እንደወጣ ጣሪያዎች ባሳለፉት ውሳኔ ይህ አዋጅ ከሥራ ላይ ከዋለ በኢትዮጵያ የፋሺዝም ስርዓት ይነግሳል ብሉ ነበር::የዲሞክራሲያ ቡድን ይህን አቋም በአገብሶ ገረፍ አድርጉ ሲያልፍ እዚሁ ቁጥር 26 ላይ፣ፋሺዝም:—

''መሬት ላራሹን፣ማምረቻዎችን መውረስ...የሚባሉትን መፈክሮች በወጣትነቱ ዘመኑ በየሃገሩ አምኖበታል፣ያወደባቸውም በታዎች አለታጡም::''

ብሏል::ባጭሩ፣መሬት በደሃ ገበሬዎች እጅ ማስገባትን የመሰለ የአዲሱ ዲሞክራሲያዊ አብዮት እምብርት የሆነ የፖለቲካ ድርጊት ፋሺዝም ነው ሲሉን ነው::ከዚህ አባባልም ፊት ለፊት ያልተነገረን መደምደሚያ ገለጽ ነው::አርሶአደሩ መሬት አግኝቶ ፋሺስት ከሚሆን፣ወይም ፋሺዝም በኢትዮጵያ ከሚነግስ፣መሬቱ ለነአስፋወሰን ይመለስና አርሶአደሩ 'ተራማጅ' ጭሰኛ ይሁን ነው::

ለነገሩ ያህል ግን፣ታሪክን እንዲህ በቀጥታ ካስኬዱት አይቀር እስቲ መሬትን አራሹ አርሶአደር እጅ ያስገባ ፋሺስት መንግስት ለጥቆ መድሃኒት ይጥሩልን::እና በፋሺዝምና 'መሬት ላራሹ' መካከል ግንኙነት ቢታየን፣በቪየትናምና በመጠኑም ቢሆን በቺሊ፣በኢንዶኔዥያ፣በብራዚል..የተቋቋሙት ፋሺስታዊ ስርዓቶች መሬትን አራሹ እጅ ሲያስገቡ ሳይሆን መሬትን እየነጠቁ ...ለከበርቴዎች ሲያስረክቡና ይህንን የሚቃወም ገበሬ ሁሉ 'ኮሙኒስት' እያሉ ሲጨፈጭፉ ነው::እንግዲህ፣ዛሬ በኢትዮጵያ በአብዮታዊው የመሬት አዋጅ በመመርኮዝና እርሱንም ከሥራ ላይ ለማዋል በሚሊዮን የሚቆጠሩ አርሶአደሮች በ21ሺህ የገበሬ ማህበራት ውስጥ ተደራጅተው በመታገል ላይ ናቸው::ከዚህ በኋላ አገራችን ፋሺስታዊ አገዛዝ ቢወድቅባት፣የኢትዮጵያ ጭቁኖችና ተራማጆች በከሃዲዎች ምሁራን ተወናብደው 'ና ጠላት ደርጉ ነው በሚል ፈሊጥ ከመሳፍንቱና ከነሲአይኤ ጉን ተሰልፈው የነዚህን ፀረ ሕዝብ ኃይሎች ሥልጣን ላይ መመለስ ያገዙ እንደሆነ ብቻ ነው::ይህንንም የምንለው የዲሞክራሲያን ቡድን ለማጋጋት ያህል እንጂ ዲሞክራሲያ ሰፊውን ሕዝብና ተራማጆቹን ከቅልባሾቹን ለማሰለፍ ያደረገው ተከታታይ ሙከራ እንደከሸፈ ለሁሉም ገለጽ ነው::

ፀረ ሕዝብ ኃይሎች አብዮታችንን ቀልብሰው ሕዝቡን ቀድመው ደርጉንከታኩ፣ያን ጊዜ እውነትም አዋጁን ለመቀልበስ፣የኢትዮጵያ ጭቁ ሕዝቦች እስከሁን የተጎናፀፏቸውን ድሎች ከመዳፋቸው ፈልቅቀ ለመንጠቅና ወደጨለማው ስርዓት መልሶ ለመጨመር፣በመንቃት ገስጋሴ ላይ ያለውን ሰፊ ሕዝብ ለማፈን፣የገበሬ ማህበራትን ለመበተን፣ባለርስቶችን መልሶ ለመትከል፣ባለፋብሪካውን መልሶ ለማንገስ፣ለአከራዩ የቤቶን ቁልፍ ለማስረከብ...የሚፈልግ መንግስት ታጋዩን ሕዝብ ምንም ዓይነት ምህረትና ርኅራኄ በሌለው አመጽና ሽብር ብቻ አንበርክኮ ለመግዛት የሚሞክር፣ከሃዲ ንዑስ ከበርቴዎች በፊታውራሪነት የሚሳተፉበት ፋሺስታዊ አገዛዝ ሊመሰረት ይችላል::ይህ በቪየትናም፣በኢንዶኔዥያ አሁን ደግሞ በቺሊ የታየ ትምህርት እንጂ በጥቂት ምሁራን አንጎል የተፈጠረ፣'ጅር ዲ ሁንዲሳ' የተባለ አድሃሪ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ እንዳለው 'ማስበርገጊያ ቃል' አይደለም::ተራማጆችን የሚያሳስበ 'ፋሺስታዊ ስርዓት የሚያንሰራራው ያሁኑ አብዮታዊ ትግል ሲቀለበስና የዛሬ 'ፀረ ፋሺስቶች' ሥልጣን ሲጨብጡ ነው::

ባጭሩ፣የዛሬው የኢትዮጵያ አብዮታዊ ትግል ተራማጅ የሆነ ኢኮኖሚያዊ መሰረት አለው::በነዚህ አዋጆች መሰረትነት እርግጥ በመሳፍንቱና በነሲአይኤ ላይ 'ጨካኝና አብሪተኛ'...ል ስርዓት ይመሰረታል::ነገር ግን ከዚህ የእንቅስቃሴው ተራማጅ የኢኮኖሚ ይዘት ተነስቶ በኢትዮጵያ 'ፋሺዝም ነገሰ' ማለት እነአስፋወሰንን ከመሰሉ ፋሺስቶች ጋር ተዳብሎ እነዚህን ተራማጅ ኢኮኖሚያዊ እርምጃዎች ለመቀልበስ ለመመቻቸት ነው::የዲሞክራሲያ ከሃዲዎች የአብዮታችንን ተራማጅ የኢኮኖሚ ይዘት 'የፋሺዝም የኢኮኖሚ ይዘት ነው' ለማለት ዳር ዳር አሉ.እንጂ ደፍረው በገለጽ አላስቀመጡትም::ስለዚህ የመጀመሪያው ጥቀስ ውስጥ እንዳነበነውም፣ቀድሞ 'ፋሺዝምን ጭካኔና አብሪተን' በሚያመለክተው መልኩ ብቻ ሳይሆን 'ውስጣዊ ይዘቱ' ትርጉሙን እናሳያለን ብለው

ቢሞክሩም፣ስንት ገጽ ሙሉ በሆነ ባልሆነው ድጋፋታ አንባቢን ካደናገሩ በኋላ፣ከሳይንሳዊ ትንተና እንደዋዛ ሊሰናበቱ ሲሞክሩ እንደዚህ እያሉ ያሾፋሉ::

‘‘...ፋሺዝምን ሲያዩ መለየት ብቻ አይበቃም::ውስጣዊ ይዘታዊ መንስኤዎቹንም ጭምር ማፍረጥረጡን ለማግኘት አስፈላጊ ነው::እዚህ ላይ ፋሺዝም መሰረቱ ምንድን ነው? የመደብ ይዘቱ ምንድን ነው? ፋሺዝም ሊመጣ የሚችለው ምን ዓይነት ኢኮኖሚያዊ፣ፖለቲካዊና ሶሺያል ሁኔታዎች ሲፈጠሩ ነው? በሃገራችን ላይ ይህ ዓይነቱ አረመኔያዊ ስርዓት እንደምን ሊወድቀባት ቻለ? የሚሉና እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች መቅረባቸው አይቀርም::መመለስ ይገባቸዋል::በቦታ ጥበት ምክንያት አሁን ባንወያይበትም ወደፊት በየተራ ማቀረባችን አይቀርም::’’

እና ‘ሳናውቀው እንዴት አረመኔያዊ ስርዓት ባገራችን ላይ ሊወድቀባት ቻለ በሚል የፈጠራ ጥያቄ ጭንቅላታችንን አንፈልጥም::የሚገርመን ግን የኢትዮጵያ ተራማጆች ምን ያህል ዳተኛ ብንሆን ነው እንደ ዲሞክራሲያ ያለው የከሃዲ አድሃሪያን ቡድን በአድሃሪነቱ ሳይጋለጥ፣በኢትዮጵያ ሕዝቦች ትግል ሳይተፋ ብዙ ጊዜ ሊቆይ ቻለ የሚለው ጥያቄ ነው::እንዲያው ለነገሩ ግን የነዚህን የከሃዲ ምሁራን ‘የተንዛዛ ችሎታ’ የማያውቅ ታዛቢ ዛሬ ‘ቦታ ጠበበን’ሲሉ ለነሱው እንደሚያፍር ይሰማናል::እና ግን፣ማርክሲስት ነኝ እያለ ከአንድ ዓመት ተኩል በላይ ሲያወናብድ የቆየ አድሃሪ ያወጣው ታክቲክ በሳይንሳዊ ትንተና ላይ የተመረኮዘ መደገፊያ እምጣ ሲባል ‘ቦታ ጠበበኝ’፣‘ወደፊት በየተራ’ እያለ ማቄን ጨርቄን ሲል እንዲህ ዓይነቱን አገሬ እውቅን እያደነቀን ከት ብለን ከመሳቅ ሌላ ምርጫ የለንም::እርግጥ ማርክሲስትም ሆኖ ሰው ቦታ ሊጠበው ይችላል::ግን በርግጥ ማርክሲስት ከሆነ የላይ የላዩን ‘ትንተና’፣በደርጉ ‘ጭካኔና አብዮት’ ላይ ብቻ ማተኮርን ለነአስፋ ወሰን/መንገሻ ሥዩም ትቶ እሱ ለሳይንሳዊ ትንተና ቦታ መስጠት ነበረበት::

ነገር ግን፣በአብዮቱ ዋና ዋና ጥያቄዎች ላይ በሙሉ ከመሳፍንቱና ከአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች ጋር የቆሙት፣የውጭ ክንፋቸው ነኝ የሚለው ንቅናቄ የመሬቱን አዋጅ ይቀለበስ ብሎ ሸንጡን ገትሮ ሲታገል ‘ተው’ ያላሉ ከሃዲ ምሁራን በትንተና ስልታቸው ብቻ ተንጠልጥለው ማርክሳዊ የሚሆኑበት ምንም ተአምር የላቸውም::ስለሆነም የደርጉን ፋሺስትነት እናስረዳለን ሲሉ ልክ አድሃሪዎች እያነሱ የሚጥሏቸውን ነጥቦች ከማስተጋባቱና አመጽን በደፈናው፣ፕሮፓጋንዳን በደፈናው፣የዲሞክራሲን መጥፋት በደፈናው፣የሀገር ፍቅርን ስሜት በደፈናው ከማውገዝ አልፈው ስለ ነዚህ ጉዳዮች ሳይንሳዊ ትንተና አያቀርቡም::ኪሳራ ማለት ይኸ ነው::

ለምሳሌ፣የዲሞክራሲያ አድሃሪዎች ቡድን ደርጉን ፋሺስት ነው ብሎ ሲወነጅል የሚጠቅሰው አንዱ ምክንያት ‘በመሰረቱ ፋሺዝም ፀረ ዲሞክራሲነት ነው’ የሚል ነው::የዓለም ፀረ ኮሙኒስቶች ሁሉ፣ከሲአይኤ እንስቶ እስከጳጳሱ፣ፊውዳሉ፣አድሃሪው ምሁር፣ከበርቴው ለዘብተኛው ተራማጅ፣ከሃዲው ‘ሶሺያሊስት’ ድረስ ተረብርቦ ኮሙኒዝም ላይ ሲነሳ፣‘በመሰረቱ ኮሙኒዝም ፀረ ዲሞክራሲነት ነው’ እያለ ነው::ስለዲሞክራሲያዊነትና ስለፀረ ዲሞክራሲያዊነት በደፈናው ማውራት የወዛደር ፓርቲ ልዩ ምልክት አይደለም::የርሱ ልዩ ምልክት ዲሞክራሲ ና ፀረ ዲሞክራሲንባለ ቋጥር ጥያቄውን ከመደብ አንፃር መመልከቱ ነው::በአገራችንም፣ደርጉ ሥልጣን ላይ ከወጣ ወዲህ የኢትዮጵያ አብዮት ጠላቶች የኢኮኖሚ ብዝበዛ መሰረታቸውን ተነጥቀዋል::የፖለቲካ መብታቸውን ተገፈዋል::ፀረ ዲሞክራሲ ሰፍኖባቸዋል::በሌላ በኩልም ለትግሉ እድገት በሚያስፈልገው መጠን ለሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች አልተከበሩለትም::በዚህን ሁኔታ፣ሃቀኛ ተራማጆች ደርጉ በሕዝብ ጠላቶች ላይ የዘረጋውን ፀረ ዲሞክራሲያዊነት እንዲገፋበትና እንዲያጠብቀው፣የነጠቀውን የሰፊው ሕዝብ መብት ደግሞ እንዲለቅ ይታገላሉ::በደፈናው የደርጉን ፀረ ዲሞክራሲያዊነት ማውገዝ በዚህ ፀረ ዲሞክራሲያዊነት ይበልጥ ከተጐዱቸው የሕዝብ ጠላቶች ጐን መሰለፍ ነው::የጭቁኖችን አምባገነንነት በቀዳሚያ ለመቃወም መሰናዳት ነው::

ከሃዲዎቹ ፀረ ሳይንስ ትንተናቸውን ሲቀጥሉ የፋሺዝም ሌላው መለዮ ‘‘ኃይልን እንደዋይነተኛ መሳሪያ አድርጉ መጠቀም ነው’’ የሚል ፀረ አመጽ ፀረ ሳይንስ የሆነ ሃሳብ ይሰነዝራሉ::ይህም ቢሆን ሲያንስ ወርሶ ትርጉም የሌለው የቃላት ቅጥጥል፣ቢበዛ ደግሞ /ያውም በዛሬይቱ ኢትዮጵያ፣ያውም ጭቁኖች ከዳር እስከዳር እስታጥቀን እያሉ በሚጮሁበት አብዮታዊ ወቅት/ ጭልጥ ያለ ፀረ አብዮትና የክህደት ፕሮፓጋንዳ ነው::እናንተ ከሃዲዎች ሌኒን ‘መንግስት ማለት የተደራጀ ዓመጽ/ኦርጋናይዝድ ቨዮለንስ/ ነው’ ያለውን የት ጣላችሁት? በአሁኑ ጊዜ ኃይልን ማውገዝ አብዮቱን ማውገዝ እንደሆነ እንዴት አጣችሁት በመሰረቱ ማንኛው መንግስት ነው፣የትኛው ስርዓት ነው፣መደብ የሚባል ነገር፣መንግስት የሚባል ‘የተደራጀ የጭቆና መሳሪያ’ ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ ‘ኃይልን እንደዋይነተኛ መሳሪያ’ አድርጉ የማይጠቀም::እንደማንኛውም መንግስት ደርግም በኃይል ይጠቀማል::ይህም በተለያዩ ጊዜያቶች የተለያዩ መልኮች ወስዷል::እንዳንድ የደርግ አድሃሪ አባሎች በየክፍለ አገራቱ ሲዞሩ በተነጥሎ በሰፊው ሕዝብ ወገኖች ላይ የኃይል እርምጃ አስወስደዋል::በመንግስት ደረጃም ተራማጆች የተገደሉበት፣የታሰሩበት ጊዜ አለ::በሌላ በኩል ደግሞ በፀረ ሕዝብ ኃይሎች ላይ ከፍተኛ የኃይል እርምጃዎች ተወስደዋል::ከፊውዳሉ ያሁሉ የኃይለ ሥላሴ ቀኝ እጆች እንስቶ በየጫካው ሸፍተው አብዮቱን ለመቀልበስ እስከተነሳሱት ባላባቶች ድረስ በደርግ ጡንቻ የተደቆሱ ብዙ ናቸው::እስር ቤት ‘‘የሚማቅቁት’’ የሕዝብ ጠላቶችም እያሌ ናቸው::አብዮታውያን ታዲያ የደርግን ኃይል መጠቀም በደፈናው አይቃወሙም::ይህንን ለአናርኪስቶችና ለከሃዲዎች ትተው መንግስቱ በሰፊው ሕዝብ ወገኖች ላይ ክንዱን እንዳያነሳ፣በፀረ ሕዝብ ኃይሎች ላይ ግን እንዲያውም በይበልጥ ኃይል እንዲጠቀም ይታገላሉ::ለዚህም መንግስት ብቻ ሳይሆን ሰፊውም ሕዝብ በዚህ በፀረ ሕዝብ ኃይሎች ላይ በሚደረገው አመጽ መሰረታዊውን ቦታ እንዲይዝ ‘ሰፊው ሕዝብ ይታጠቅ’ ይላሉ::እያችሁ እናንተ ከሃዲዎች፣ደርጉ በኃይል መጠቀሙን በደፈናው እስከተቃወማችሁ ድረስ፣በውጭ አገር ያለው ተጠሪያችሁ ‘የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ ይፈቱ’ የሚል አቋም እስኪያስተጋባላችሁ ድረስ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ እነ ሲአይኤ እነ አስፋ ወሰን ሁሉ አብረዋችሁ

ይሰለፋሉ፡፡እንደኛ ግን በሰፊው ህዝብ ወገኖች ላይ የሚደረገውን አመጽ ብቻ ብተቃወሙና ተራማጅ
የፖለቲካ አስረኞች ይፈቱ ብትሉ ኖሮ አሁን የሚያደርጉላችሁን ማንከባከብና ድጋፍ ትተው ባይናች
ሁን ላፈር ይሏችሁ ነበር፡፡

የዲሞክራሲያ ከሃዲዎች ሌላ የፋሽዝም ''ጨካኝና አብሪተኛ'' መልክ ብለው የሚያቀርቡት
''የፋሽዝም አገዛዝ ግመሣሪያ ኃይል እንደበተረመንግሥት በቀኝ እጁ ጨብጦ በግራ እጁ የሚጨብጠ
ው ፕሮፓጋንዳ ነው'' የሚል ነው፡፡እዚህም ላይ በደፈናው የቀረበው የከሃዲዎቹ አቋም ከነሲአይ
ኤ ፀረኮሙኒስት ፕሮፓጋንዳ ጋር እንደሁለት ጠብታ ውሃ ይመሳሰላል፡፡በመሠረቱ ማንኛውም ሥርዐት
በፕሮፓጋንዳ ይጠቀማል፡፡ ነገር ግን ከማርክሲስቶቹ በስተቀር ሌሎች ኃይሎች በሙሉ በኃይልና በፕ
ሮፓጋንዳ መጠቀማቸውን ዘለዓለም እንደካዱ ናቸው፡፡ስለሆነም ፕሮፓጋንዳ ያረገ ሁሉ ፋሺስት ነው
ማለት የአብዮታዊ ፕሮፓጋንዳን ተቃውሞ ፀረአብዮት ፕሮፓጋንዳ መንፋት ነው፡፡እንዲያውም፤ከኢትዮ
ጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ይህንን የዴሞክራሲያ አድሃሪዎች ተቃውሞ ብንመረምር አድሃሪነቱ የ
በለጠ ግልጽ ይሆናል፡፡ የደርጉ ፕሮፓጋንዳ በየጊዜው የተለያዩ ይዘቶች እንደነበሩዋቸው ግልጽ ነ
ው፡፡ከነዚህም ይዘቶች አንዳንዶቹ አድሃሪ ነበሩ፡፡በጠቅላላው ሲታይ ግን በዘመነ ኃይለ ሥላሴ
ይነዛ ከነበረው አደገኛ ፕሮፓጋንዳ ጋር ሲወዳደር ተራማጅና ፀረ ፊውዳል ይዘቶች ነበሩት፡፡በ
ዚሁ የደርግ ፀረ ፊውዳል ፕሮፓጋንዳ የተሸበሩ ጳጳሳትና መሳፍንት እንደሚያደርጉት፤የኢትዮጵያ
ሃቀኛ ተራማጆች የደርጉን ፕሮፓጋንዳ በንቀትና በማጥላላት ሊመለከቱት አይችሉም፡፡ ተራማጅ ይዘቶ
ቹን መደገፍና ማጉላት፤አድሃሪ ይዘቶቹን መተቸትና ተከከለኛውን አስተሳሰብ ማሳየት ግዴታቸው ነ
ው፡፡ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የደርጉ ፕሮፓጋንዳ አድሃሪ ይዘቶች እየጠፉ፤ብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ
አብዮትን የተንተራሱ ይዘቶች እየጨመሩ በመሄድ ላይ ናቸው፡፡በአጠቃላይ ፀረ ፕሮፓጋንዳ አቋም
ከመውሰድ አልፍ ዛሬ የደርግን ፕሮፓጋንዳ በደፈናው መቃወም፤የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ ንቃተ ሕሊ
ና መጉለመስ መቃወም፤ስለዚህም በፊውዳሊዝም ርእዮተ ዓለም ላይ የተከፈተው ጦርነት እንዲቆም
መታገል ነው፡፡

የዲሞክራሲያ አዘጋጆች የፋሺዝም ልዩ ጠባይ ብለው ካቀረቧቸውና በፀረ አብዮት ፕሮፓጋን
ዳ ላይ እንደተሰማሩ ከሚያስነቃባቸው ሌላኛው ነጥብ፤'አክራሪ ብሄራዊ ስሜትን እንቃወማለን' የሚ
ለው ነው፡፡ይህን ሲሉ የደርጉን 'አክራሪ ብሄራዊ ስሜት' አብዮታዊ በሆነ የሃገር ፍቅር ስሜት
ለመተካት ሳይሆን ለያዙት ንግድ እንዲያመቻቹ ብቻ የተወሰደ አቋም እንደሆነ ዝቀ ብለን እናሳያለ
ን፡፡የከሃዲዎቹ የሃገር ፍቅር ከነአሰፋ ወሰን የሃገር ፍቅር የተመሳሰለ ነው፡፡የሁለቱም ፍልስ
ፍና''ከሞተቹ ሚስቴ ምን አለኝ ከማቴ'' የሚል ስለሆነ፤የመደብ ጥቅማቸው ስለተነካ ፡'ምን'አለን
አገር'ብለው ያከትማሉ፡፡ከዚያ ወዲያ፤ቀንጣትም ትሁን የሃገር ፍቅር ስሜት፤'እናት አገር''አበ
ት አገር'ያለ ወዩለት!'ለፋሺስትነቱ ተጨባጭ መረጃ ይዞ ተጋለጠ ማለት ነው፡፡በአገር ፍቅርና
በአብዮታዊ ትግል መሃል ስላለው የተቀራረበ ግንኙነት ወደፊት በሰፊው እንመለስበት ይሆናል፡፡አ
ሁን ግን ሁለቱ ተደጋጋፊ እንጂ ተቃራኒ እንዳልሆኑ የነሆቺሚንን ስም ብቻ ጠቀስን እንለፍ፡፡
ነገር ግን እነዚህ ከሃዲዎች ነገሩን ጠለቅ ብለው እንኳ ሳይመረምሩ' ሂትለር አባት አገር ሲል
ምርጦቹ እናት አገር ይላሉ' ሁለቱም ፋሺስቶች ናቸው'ብለው ሲናገሩ እነሌኒን እነስታሊን 'አባት
አገር''እያሉ ሕዝብን መቀስቀሳቸውን ከማን ለመደበቅ ነው?ወይስ የኛ'ማርክሲስቶች'ይህቹንም
ሀቅ አያውቋት ይሆን?

የዲሞክራሲያ አዘጋጆች በዚህ ጉዳይ ላይ በአቋም ሲቸበቹቡ የሚያዙት ለጭቁን ሕዝቦችዋ
ሰብአዊ ክብርና ዋጋ ያለው ኑሮ ለማስገኘት ለሚታገለውና የአካባቢው አድሃሪያችና ኢምፔሪያሊ
ስቶች የሚጠነስሱባትን ሴራ ለመቋቋም ለምትተናነቀ ሃገራችንን እንደ ሂትለር ጊዜ ጀርመን አድር
ገው ሲያቀርቧት ነው፡፡ደርጉ 'የመስፋፋትና ሌሎች ጉረቤት ሕዝቦችን የመውረር ስሜት እንዳለው
ይነግሩናል፡፡በነሱ አባባል ደርጉ ''እኛን ለማጥፋት በሚደልቱ ታሪካዊ ጠላቶቻችን የተከበብን
ስለሆንን ሳንቀደም መቀደም አለብን ባይ ተጋዳይነት ይሆናልበማለት ሕዝብን ጦር እንዲናፍቅ፤ባይ
ኑን ወደውጭ እንዲተክል'' ያደርጋል ብለው ለዚህ ተጨባጭ መረጃ 'ሂትለር ስለሩሲያውያን፤ምርጦቹ
ስለአረቦችና ስለሱማሌዎች' ያላቸውን አስተሳሰብ እያመሳሰሉ ያቀርቡልናል፡፡

እዚህ ላይ ብዙ ብዙ የሚያጽፈን ነገር ነበር፡፡በደፈናው ግን አንዳንዱ ነገሮችን ብቻ ጠ
ቅሰን እንለፍ፡፡አረቦች በደፈናው፤ሶማሌዎች በደፈናው ጠላቶቻችን ናቸው አንልም፡፡ ነገር ግን ደ
ግሞ ያለውን አንዳንድ ሃቅ አፍረጥርጦ ለመናገር የሚያስረን፤ምንም በአድርባይነት የሚያናግረን
ሁኔታ በሌለ ቸብቸባና ንግድ የሌለበት ግልጽ አቋም እንገልጽ፡፡ የኢትዮጵያ አብዮት ከጉረቤት
አድሃሪዎች አደጋ የለበትም ብለን ጭቁን ሕዝቦችን ለማዘናጋት አንሞክርም፤አለበት፡፡በሰሕድ ቁጥ
ር 37 ላይ በሚገባ እንደገለጸነው አድሃሪ የአረብ መንግስታት ከኢትዮጵያ ፀረ አብዮት ኃይሎች
ጋርና ከዓለም ዐቀፍ ኢምፔሪያሊዝም ጋር በሃገራችንና በአብዮታችን ላይ ያሴራሉ፡፡ለዚህም የሚገ
ባው አፀፋ፤ከጉረቤት አገሮች አብዮታውያን ጋር በኢንተርናሺናሊዝም መንፈስ የጠበቀ አንድነት
መስርቶ አድሃሪ ኃይሎችን መቋቋም ነው፡፡አገራችንና አብዮታችን ላይ ያለውን ይህን የጉረቤት አ
ገሮች አድሃሪዎች ሴራ መካድ ወይም መደበቅ የደርጉን ብሄረተኛነት መቃወም ወይም ከጉረቤት አገ
ሮች ተራማጆች ጋር መተሳሰር አይደለም፡፡ከአድሃሪዎች ጋር ተደባብሎ የኢትዮጵያን ጭቁኖች አዘናግ
ቶ በጠላት እንዲመታ ማድረግ ነው፡፡

የዲሞክራሲያ አድሃሪዎች ዞር ዞር ደርጉን 'በአክራሪ ብሄራዊ ስሜት'ይከሳሉ እንጂ እ
ነሱ የአድሃሪ ጉረቤት አገሮች መንግስታትን ፀረ አብዮት ሴራ ለመሸፈን ሲሞክሩ 'የአክራሪ አድ
ርባይነት ስሜት'አባዜ እንደያዛቸው ግልጽ ነው፡፡ለዚህ ምሳሌ እንዲሆን 'ሰው ሳይሰማ'በውጭ አ
ገር ለአንድ 'አፍሪክ አዚ'ለተባለ የሲአይኤ ጋዜጣ በሰጡት ቃለ መጠይቅ/ኢንተርቪው/ ላይ አን
ዷት እንደሚነገቁ ለማሳየት እንጥቀስ፡፡

የዲሞክራሲያአድሃሪዎች ከጥቂት ሳምንታት በፊት ለዚህ አፍሪክ አዚ ለተባለ 'የነፃ አ
ድሃሪ'ጋዜጣ ቃለ መጠይቅ ሰጥተው ነበር፡፡ የዚህ ቃለ መጠይቅ ዓላማ የሃገራችንን አብዮት በዓለ
ም ተራማጆች ፊት ሆን ብሎ ለማጥላላትና ከዓለም ተራማጆች ለመነጠል ብቻ ሳይሆን ለኢህአፓ ከአ
ረብና ከጉረቤት አገሮች ድጋፍ ለመሰብሰብ እንደሆነ ከይዘቱ ግልጽ ሆኖ ይታያል፡፡

በዚሁ ኢንተርቪው ውስጥ፣የኢህአፓ ቃለ አቀባይ ነኝ የሚል ሰው፣ስለመሬት አዋጅ ወር
ቦ ሥራ ላይ አለመዋሉና 'ስለመዋቱ'፣ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ የኢምፔሪያሊስቶች ዋና ምሽግ
ስለመሆኑ፣በዓለም ፖለቲካም ከኢምፔሪያሊስት ቡችሎች ከነደቡብ አፍሪካ ጋር አንድ ለአንድ ተያ
ይዛ የቆመች መሆንዋን ጠቅሶ እንደሚከተለው ይደመድማል::

''በጂቡቲ ጉዳይ፣በስፓኒሽ ሰሃራ ጉዳይ የኢትዮጵያ መንግስት ከደቡብ አፍሪካ፣ ,..ተ
ከሞቡቱና ከንጉስ ሃሰን ጋር ተሰልፏል::''ይላል::

ነገር ግን፣ማንም ሃቀኛ ተራማጅ እንደማይስተው፣የኢትዮጵያ መንግስት በጂቡቲም ሆነ
በስፓኒሽ ሰሃራ ጉዳይ ብሄሮች የራሳቸውን እድል በራሳቸው ለመወሰን ያላቸውን መብት የሚያው
ቀ ነው::የዲሞክራሲያ አቋም ግን ለገበያ እንዲመች ሆና የተወሰደ አቋም ነው::በጂቡቲ ጉዳይ
የደርጉን አቋም የለለ ሰበብ እየሰጠ በመቃወም በዚሁ ጉዳይ ላይ አድሃሪ የመስፋፋት አቋም የ
ወሰደቸውን ሱማሊያን ይደግፋል::በስፓኒሽ ሰሃራ ጉዳይ 'እንዳጋጣሚ' የብሄረሰቦችን መብት ማወ
ቀ ለገበያው የሚያዋጣ በመሆኑ እዚህ ላይ ንጉሥ ሁሴንን ተቃውሞ ከደርጉ ጋር ከስፓኒሽ ሰሃራ
ሕዝብ ጎን ተሰለፈ::ግን አሁንም ለገበያው እንዲመቹ፣'በመሰ ኢትዮጵያ ያለኗቸሁ እኔ ነኝ'
እያለ ለሚያንቦለብለው ቸብቻብና ፕሮፓጋንዳው እንዲመቹ፣የደርጉን አቋም ሸፍጥ በተመሳሰት አድ
ርባይነትና ዉርስ ዓይነ ባለሸ ማጭበርበር አጣሞ 'ደርጉ በንጉስ ሀሰን ጎን ተሰልፏል'ብሎ የ
ሌለ አቋም ይሰጠዋል::ይሽ ታዲያ የደራ ንግድ ማካሄድ ነው?ወይስ ለኢትዮጵያና ለአፍሪካ ጭቆ
ን ሕዝቦች ነፃነት መቆም?!

ለመደምደም ያህል፣የዲሞክራሲያ መሪዎች ደፍረው እንደማይመልሱ እያወቅን፣አንዳንድ ጥያ
ቄዎችን አስቀምጠን ለማጠቃለል እንወዳለን::

አንደኛ::መኢሶን እስከዛሬ ድረስ የኢትዮጵያን አብዮት በሚመለከቱ ዋና ዋና ጥያቄዎች
ላይ በሙሉ ግልጽ የሆነ አቋም እየወሰደ መጥቷል::አድርባይ ብትሉት፣ወላዋይ ብትሉት፣የፈለጋች
ሁን ብትሉት ከነዚህ አቋሞች አንደኛቸውም ቢሆኑ ከኢትዮጵያ ሕዝቦች ቀንደኛ ጠላቶች፣ከነአስፋ
ወሰን/መንገሻ ሥዩም፣ከመሰፍንቱና ከነሲአይኤ ጋር አላዳበሉትም::እንዲያውም ከቅርብ ጊዜ ወዲ
ህ ድርጅት እየተጠናከረ ስለመጣ፣የነመንገሻ ሥዩምና የሲአይኤ ጋዜጦች በዚህ ድርጅት ላይ ይህ
ነው የማይባል የማጥላላት ዘመቻ ይዘው እናያለን::እናንተን ነበሚመለከተው ግን ጠርሶ የተገላቢ
ጦሽ ነው::በመንግስት ጥያቄ፣በዲሞክራሲ ጥያቄ በወጣቶች ዘመቻ ጥያቄ፣በደርጉ ባህርይ...በጠ
ቅላላው የኢትዮጵያን አብዮት በሚመለከቱ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ በሙሉ ከነዚህ የሕዝብ ጠላቶች
ጋር አንድ ዓይነት አቋም እየወሰዳችሁና እየተጋለጣችሁ ይሽው እዚህ ኪሳራ ደርሳችኋል::ይህ
የአቋም አንድነት 'የአጋጣሚ'ይመስላችኋል? መኢሶንን የሚያንቋሽሹ የኢምፔሪያሊስት ጋዜጦች እ
ናንተን ያሞግሳሉ::ይህስ 'የአጋጣሚ'ይመስላችኋል?የሲአይኤ ተብለው ለታወቁ እንደ አፍሪክ እ
ዜ ዓይነት ጋዜጦች አርማችሁ ያለበት ኢንተርቪው ትሰጣላችሁ::እነዚህ ጋዜጦች የናንተን ሃሳብ
ለማስፋፋት የሚፍጨረጨሩት ለምን ይመስላችኋል?እስቲ ለኢትዮጵያ ተራማጆች ፊት፣ተራማጅ መስላች
ኋችው በሚከተሉዋችሁ ወጣቶች ፊት እነዚህን ጥያቄዎች መልሱ!!

ሁለተኛ::በሃገር ውስጥ የምታሳዩት መልክና በውጭ አገር የምታሳዩት መልክ እንደ ቀይና
እንደ ነጭ የተለያየ ነው::በውጭ አገር፣የኢህአፓ ተጠሪ ነኝ እያለ የሚያወናብደው፣ገንዘብ የሚ
ሰበስበው፣ፕሮግራማችሁን የሚያሰራጨው 'ዓለም ዐቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን' የተባለው
ድርጅት ነው::ይህ ድርጅት ተራማጅ መስሎ በቃላት ድንፋታ ብቻ የኢትዮጵያን ተማሪዎች ለመከፋ
ፈል ብዙ ጥረት ካደረገ በኋላ በሃቀኛ ተራማጆች ከፍተኛ ትግል ተጋልጧል::የናንተንና የመሳፍ
ንቱን አቋም ሙሉ በሙሉ ይዞ፣'በተጨማሪ'እንደናንተ ዳር ዳር ማለት ሳይሆን የመሬቱን አዋጁን
ተቃውሞ፣እንዲያውም መሬት ወደግል ሃብትነት እንዲመለስ በግልጽ እየተከራከረ ነው::መረጃዎች
ካላችሁ እናቀርባለን::በውጭ አገር ያሉ ተራማጅ ኢትዮጵያውያን 'የመንገሻ ሥዩም/አስፋ ወሰን
የወጣቶች ድርጅት'ይሉታል::እሱ ደግሞ የኢህአፓ ነኝ ይላል::እናንተ ውጭ አገር በምታትሙት
'አብዮት' የተባለው የእንግሊዝኛ ጋዜጣችሁ አብዮታዊ ድርጅት እያላችሁ ትከቡታላችሁ::ይህን
ድርጅት 'አብዮታዊ'ስትሉ እንደዲሞክራሲያ ዓይነቱን ''አብዮታዊነት'' ነው?ወይስ በ1968
ኢትዮጵያችን 'የማንን እርስት ለማን' እያለ የሚደነፋ የመሳፍንት ርዝራዥ ሁሉ ገና ለገና
ወጣት ነው፣ገና ለገና እነሌኒንን ጠቃቅሷል ተብሎ አብዮታዊ የሚባልበት ተዓምር አለ?እስቲ
በዚህ የነአስፋ ወሰን/መንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅትና የናንተ የውጭ ተጠሪ ነኝ በሚል ድር
ጅት ላይ ያላችሁን አቋም ለኛ እንኳ ሳይሆን ለአባሎቻችሁ ስትሉ አብራሩ!
በሉ ለዛሬ ይበቃን::እናንተ ዝም ብትሉም እንመለስበታለን::

ከሃዲ ምሁራን ይውደሙ!!

ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!!